# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
## UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት
UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES

ቀን 16/2/98
Date
ቁጥር ኢዴኃኅ/ፀጽቤ/251/98/05
Ref.No

ለኢዴኃኅ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት
በያሉበት

**ጉዳዩ፣ <u>በኢዴኃኅ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስም ጥቅምት 14 ቀን 1998 ዓ.ም በቁጥር ኢዴኃኅ /ሥ.አ/1/98 ስለተበተነው ደብዳቤ ሕገ-ወጥነት ስለመግለፅ</u>::**

ከላይ የተጠቀሰውን ደብዳቤ የኢዴኃኅ የስራ አመራር አካል የማያውቀው ነው:: ምክንያቱም ከላይ በተጠቀሰው ደብዳቤ ውስጥ የሰፈረው ጉዳይ በአጀንዳነት ተይዞ ለመነጋገር በኅብረቱ የበላይ የሥራ አመራር አካል የተጠራ ስብሰባ ባልነበረበት ሁኔታና በህብረቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 6.2.15 መሰረት ያልተወሰነ ውሳኔ በመሆኑ ነው:: በእኛ እምነት ይኸን አፍራሽና አደናጋሪ ጽሁፍ ማሰራጨት ማንን ሊጠቅም እንደሚችል ግራ የሚያጋባ ነው:: በሕብረቱ የአሰራር ደንብ መሰረትም ሕገ-ወጥ መሆኑን ይህንን ላደረገው ወገን ማስገንዘብ እንወዳለን:: ይህንን ጽሁፍ ያሰራጨው ወገን ቁምነገር ብሎ የጠቀሳቸው፣

1. በጽሁፉ ውስጥ የተጠቀሱት የኅብረቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፆች 7.4.4 እና 7.4.5 ለጉዳዩ ተገቢነት እንደሌላቸው ለመረዳት የህብረቱ 2ኛ መደበኛ ሸንጎ ጉባኤ ለበላይ የሥራ አመራር አካሉ ብቃት የሠጠውን አድናቆት ከሰነዱ መመልከት በቂ ነው እንላለን::
2. የህብረቱ የበላይ የስራ አመራር አካል የተሰየመው በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 6.13.1.1 እና 6.13.2.1 መሰረት በብሄራዊ ሸንጎው መሆኑን የጽሁፉ ባለቤቶች መዘንጋታቸውንም ማስታወስ እንወዳለን:: ስለሆነም በጽሁፍ ያሰፈረውን እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ያለው የሰየመው አካል መሆኑን የጽሁፉ ባለቤቶች ያለማጤናቸው ገርሞናል::
3. የህብረቱ ብሄራዊ ሸንጎ ከየድርጅቱ የሚወክሉ ሁለት ሁለት አባላትን የያዘ አካል መሆኑንም በመዘንጋት፣ የአባል ድርጅቶችን የስም ዝርዝር በዋቢነት ማስፈሩ ሕጋዊነትን እንደማይሰጥ እናስገነዝባለን::
4. የህብረቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፓርላማ መግባት /ያለመግባት በሚለው ጉዳይ ላይ አባል ድርጅቶች ስለወሰዱት አቋም መስከረም 29 ቀን 1998 ዓ.ም በተላከው ማስታወሻ ገልፀናል:: ስለሆነም ዘወትር 10:ለ3 እየተባለ የሚጠቀሰው አሃዝ ሕጋዊነት የሌለው መሆኑን ደግመን ማሳሰብ እንወዳለን::

በመጨረሻም ስለኅብረቱ ሕልውናም ሆነ ስለ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል በሰከነ አእምሮ ማሰቡ እንደሚጠቅም እንመክራለን:: በኛ በኩል ሐሙስ ጥቅምት 17 ቀን 98 ዓ.ም በ11:00 ሰዓት በተጠራው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቴሌ ኮንፍራንስ ላይ በተነሱት ጉዳዮች ዙሪያ ተነጋግረን መፍትሄ እንደሚገኝላቸው ተስፋ እናደርጋለን::

ከሰላምታ ጋር

በየነ ጴጥሮስ (ዶ/ር)
የኢዴኃኅ የወቅቱ ሊቀመንበር

መረራ ጉዲና (ዶ/ር)
የኢዴኃኅ የወቅቱ ም/ሊቀመንበር

ግልባጭ፣

- ለክቡር አቶ ግርማ ሹምዬ
- አክቡር አቶ ደረጀ ከበደ
- ለክቡር አቶ ሙሉ መጃ
- ለኅብረቱ ጽ/ቤቶች
- የኅብረቱ አባል ድርጅቶች በያሉበት

**<u>ዋና መስሪያ ቤት (Main Office)</u>**
ፖ.ሣ.ቁ 24655/1000 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ ቁጥር (Tel.No.)574721 ፋክስ (Fax)251-574720

**<u>ሰሜን አሜሪካ ቢሮ (North America</u>**
5309 Georigia Ave.NW 2nd fl,"Washington, Dc 20011
E-Mial uedf addis @athionet-et
Box 18573, Addis Ababa, Ethiopia Tel.# 202-291-4217 Fax.# 202